# እቺን ጥቅስ ተጠቃሚዎች አያውቋት ይሆን ?

ቢላል አልጀበርቲ 01/17/14

ዶ/ር መረራ ጉዲና "ህይወቴና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞ" በሚል ርእስ የፃፉትን ግለ ታሪክ መፅሃፍ ከጥቂት ወራት በፊት ማሳተማቸው አይዘነጋም፡፡ ዶ/ር መረራ በዚህ መፅሃፋቸው "በዘመነ ኢህአዲግ ከአራት ኪሎው ቤተመንግስት ቀጥሎ ሰሜን አሜሪካ በተለይም ዋሽንግን ዲሲ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ማእከል ሆኗል" ሲሉ ገልፀዋል፡፡

እንደኔ እምነት ግን መላው የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ተጠቅመው ክልላዊ መንግስታትን ከመሰረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁንስ ዋሽንግተን ዲሲ የአራት ኪሎው ቤተመንግስትም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ማዕከል መሆኑ ቀርቷል፡፡

ምክንያቱም በአዲሲቱ ፌዴራላዊት ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የህዝቦች ታሪክ የፖለቲካ ስልጣን እንደ ቀደም ሲል እንደነበረው እዚህ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኘው የአራት ኩሎው ቤተመንግስት በጥቂት ፊላጭ ቆራጭ የገዢው መደብ ቁንጮዎች ችሮታ ቁልቁል የሚታደል አይደለም፡፡

የህዳሴው ዘመን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚገለፁበትን ሀገራዊ የፖለቲካ ዘይቤ ከዚህ በፊት የነበሩት የሀገራችን አሃዳዊ ስርዓተ መንግስታት ከሚታወቁበት መሰረታዊ ባህሪ ፈፅሞ የተለየ ነው፡፡ የተለየ የሚያደርገው ዋነኛ መገለጫ ያልተማከለ (decentralized) የሆነ የአስተዳደር መዋቅር ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ አወቃቀር ስልጣን አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ወደ ሚገኝበት ታዕታይ (የታችኛው) መዋቅር ይወረዳል፡፡

የተማከለ አሃዳዊ አስተዳደራዊ የመንግስት አወቃቀር ይከተሉ የነበሩ የሀገራችን ስርዓተ መንግስታት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የፈፀሙትን ታሪካዊ ስህተት ለማረምና በምንም መልኩ እንዳይደገም ለማድረግ የሚያስችል መሰረተ ፅኑ ፌዴራላዊ ሥርአት ተገንብቷል፡፡ይህ ፌደራላዊ ሥርአት ስኬታማ የሚባል ውጤት እያመጣ ባለበት አዲሲቷ

ኢትዮጵያ ለሁሉም ነገር "ከኛ ወዲያ ለአሳር ነው" የማለት አባዜ የተጠናወታቸው ጥቂት ያለፉት ስርአት ውርዴ አኩራፊ ፖለቲከኞች ባህር ተሻግረው ለዚች አገር ህዝቦች በጎ ከማያስቡ ባእዳን ሃይሎች ጋር መዶለታቸው "የኢትዮጵያ ፖለቲካ ማእከል አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ ሆኗል" ወደሚል ማጠቃለያ አያደርስም፡፡

እርግጥ ነው የ1966ቱን አብዮት ተከትሎ በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ የተስተዋለውን የነጭና ቀይ ሽብር ደም አፋሳሽ እልቂት በመቆስቆስ ረገድ የመሪ ተዋናይነት ሚና የነበራቸው ዶ/ር ነገደ ጎበዜን የመሳሰሉ ግለሰቦች ገና ከወጣትነት ዘመናቸው ጀምሮ የተጠናወታቸውን የመንግስት ስልጣን ምንተፋ በምእራባውያኑ ሃያላን መንግስታት ቡራኬ ብቻ እውን ማድረግ የሚቻል እየመሰላቸው በተለይም አሜሪካንና አንዳንድ የአውሮፓ ሀገራትን ከኢትዮጵያ ጋር ለማቃቃር ሲሉ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ ይታወቃል፡፡

እንዲያም ሆኖ ግን የዲያስፖራዎቹ ፖለቲከኞች በአንድ ወይም በሌላ አቋራጭ መንገድ ወደ ስልጣን የመውጣት ህልም ወደ ለየለት የቁም ቅዠትነት ከመቀየሩ የተነሳ የተቃውሞ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ምክንያታዊነትን ገድሎ ለመቅበር ያለመና ከጭፍን የጥላቻ ስሜት በመነጨ የዜሮ ድምር አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ተራ ክፋት እንጂ ዶ/ር መረራ ጉዲና ሊነግሩን እንደሞከሩትዋጋ የሚሰጠው ጉዳይ አየደለም፡፡

ለነገሩ ዶ/ር መረራ አንጋፋ የፖለቲካል ሳይንስ ምሁር ስለመሆናቸው ተደጋግሞ ቢነገርላቸውም፣ እርሳቸው ብዙውን ጊዜ የሚያሳዩት ባህሪ ግን ፊደል ካለቆጠረ ተራ ሰው እንኳን የሚጠበቅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ለዚህ ትችቴ ምክንያት የሆኑኝን ዋና ዋና ዶ/ር መረራ በአንደበታቸው የተናገሩዋቸውን ትዝብት ላይ የሚጥሉ ስህተቶች መሃከል የተወሰኑትን ላስታውሳችሁ ወድጃለሁ፡፡

መጋቢት 24 ቀን 2002 ዓ/ም በአዲስቷ ፌዴራላዊት ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ ልዩ ስፍራ የሚሰጠው ሀገራዊ ድል የተበሰረበት እለት እንደነበር ሁሉም ኢተየጵያዊ ያስታውሳል፡፡ የመላው ኢትዮጵያውያን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች የዘመናት ቁጭት ሆኖ የኖረው ታላቁ የዓባይ ወንዝ ውሃ ለዚች አገር የህዳሴ ጉዞ የአቅጣጫ ጠቋሚነት ሚና የሚጫወት የኤሌክትሪክ ሃይል ያመነጭ ዘንድ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ስራ መጀመር የተበሰረውና የመሰረት ድንጋይም የተጣለው በዚህ ዕለት ነበር፡፡

መንግስት ይህን የኢትዮጵያን ሕዝብ የዘለአለም ቁጭት የሻረ መልካም ዜና ይፋ ማድረጉን ተከትሎ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በየራሳቸው ቋንቋ አንድ ቃል ሲናገሩ የተደመጡበትን የድጋፍ ሰልፍ ለተከታታይ ሳምንታት ያለማቋረጥ ሲያካሂዱ መሰንበታቸው ከእያንዳንዳችን አእምሮ የማይጠፋ ልዩ ትዝታ ነው፡፡

በዓባይ ወንዝ ላይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ የሚገነባበት የመሰረት ድንጋይ የመጣሉን ታሪካዊ እውነታ እጅግ አስገራሚ ሀገራዊ ድል አድርጎ የቆጠረው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ጉዳዩ የፈጠረበትን ልባዊ ደስታ ለመግለፅ ሲል ያን ዓይነት ለጋራ ልማት የመነሳሳት ቁርጠኝነት ተላብሶ አደባባይ መውጣቱን በቀጠለበት ሰሞን ዶ/ር መረራ በጉዳዩ ዙሪያ አንድ ትዝብት ላይ የጣላቸው አስተያየት ሰጥተው ነበር፡፡

ምንም እንኳን የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ዜና መበሰሩን ተከትሎ የታየው የህዝብ ድጋፍ ያንገበገባቸው ጥቂት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እንዳልነበሩ መገመት ባያዳግትም፣ እንደ ዶ/ር መረራ ጉዲና ገመናውን አደባባይ አውጥቶ ለከፋ ትዝብት እስከመዳረግ በዘለቀ አኳኋን ሲናደድ የተስተዋለ ግን የለም፡፡

እናም ዶ/ር መረራ በሁኔታው እጅግ በመብሸቃቸው፣ በወቅቱ ስለጉዳዩ አስተያየት ሊጠይቋቸው በሔዱት የኢቲቪ ጋዜጠኞች ካሜራ ፊት መሆናቸውን እንኳን ዘንግተው "አይ የዓባይ ጉዳይ እኔን ስለማይመለከተኝ ምንም ዓይነት አስተያየት ልሰጥህ አልችልም፡፡ ባይሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የዓባይ ልጆች ብትጠይቅ ይሻላል እንጂ እኛ የለንበትም" የሚል ምላሻቸውን የሰጡበት መንፈስ እጅግ በጣም አሳፋሪ እንደነበር ማንም ተመልካች ያስታውሰዋል፡፡

ለመሆኑ ዶ/ መረራ "የዓባይ ጉዳይ እኛን አይመለከተንም" ሲሉ ምን ማለት ፈልገው ነው? እነርሱ እነማናቸው? የሚመሩትን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አቋም መግለፃቸው ነው? ወይስ ሰፊውን የኦሮሞን ህዝብ ማለታቸው ይሆንእወክላለሁ ለማለት ሲቃጣቸው ይሆን? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን እያነሳሁ በመጣል ጥቂት እንዳብሰለሰል የተገደድኩበት አጋጣሚም ነበር። እኔ እስከማውቀው ድረስ እስከዛሬ "ዶ/ር መረራ ይህን ለምን ተናገሩ?" ብሎ የጠየቀ ወይም አስተያየተ የሰጠ ሚዲያ አላጋጠመኝም፡፡

እናም ሰውየው ይሄን ሃይ ባይ የማጣት ክፍተት እንደመልካም ዕድል ተጠቅመው በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን አፍራሽ አስተያየቶች መሰንዘራቸውን ስራዬ ብለው ተያይዘውታል፡፡ ለዚህ ማሳያነት  በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል።

ለምሳሌ ባሳለፍነው 2005 ዓ/ም ግንቦት ወር ላይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሚገነባበትን ስፍራ ከውሃ ነፃ ለማድረግ ሲባል የዓባይን የጉዞ አቅጣጫ የማስቀየስ ተግባር በመከናወኑ ይታወሳል፡፡ እናም በዚሁ ምክንያት የተቆጡ አንዳንድ የግብፅ መንግስት ባለስልጣናት ሀገራችንን ለማስፈራራት ያለመ የሚመስል ውዥንብር ለመንዛት መሞከራቸውን ተከትሎ የታዘበኩትን የዶ/ር መራራ ይሉኝታ ማጣት ላካፍላችሁ።

ያኔ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ወቅታዊውን የኢትዮ ግብፅ ሁኔታ በተመለከተ ካነጋገራቸው የፖለቲካ ምሁራን መሃከል አንዱ  ዶ/ር መረራ ጉዲና ነበሩ፡፡ በዚህ አጋጣሚ በጉዳዩ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ “ግብፆች ራሳቸው ጦርነት እንደማያዋጣ ይገነዘባሉ የሚል ግምት ነው ያለኝ። የሰሞኑ ዛቻቸው እውነት ሆኖ  ኢትዮጵያን ለማጥቃት ከሞከሩ ግን እኛ ተቃዋሚዎች ከገዢው ፓርቲ ያነሰ የሀገር ፍቅር የለንም´ ሲሉ ከበፊቱ አቋማቸው ጋር የሚጣረስ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ እርግጥ ተቃዋሚዎች በአባይ ውሃና በሕዳሴው ግድብ ዙሪያ ተቆርቋሪነት ማሳየታቸውን ግን በበጎ ጎኑ ይምመለከተው መሆኑ እንዲታወስልኝ እፈልጋለሁ ።

ዶ/ር መረራን ያናገራቸው የአዲስ አድማስ ጋዜጠኛ  “እርስዎ ከዚህ ቀደም የግድቡ ግንባታ ይፋ የሆነ ሰሞን፣ የዓባይ ጉዳይ እኛን አይመለከተንም የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት? ከዚያ ወዲህ የዓባይ ልጅ መሆንዎን ተገንዝበው ነው ከሌሎችም በበለጠ ተቆረቋሪ ለማለት የበቁት?” ብሎ መጠየቅ ይጠበቅበት ነበር፡፡ ጋዜጠኛው ይህን ባለማድረጉ የዶ/ር መራራ አቋም ሳይገባን በተለመደው ተገለባባጭነታቸው ቡራቡሬ ሆነው ቀርዋል፡፡

ዶ/ር መረራ በዚህ የተዘበራረቀ ማንነታቸው ለሁለተኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ፕሬዚዳንት ሆነው መመረጣቸውን የሰማሁት በዚያው ሰሞን መሆኑ ደግሞ ይበልጥ እንድገረም አድርጎኛል።

መቾስ መድረክ ከእርሳቸው የተሻለ ሰው የለኝም ብሎ ካመነ ዶ/ር መረራን ዳግም በፕሬዚዳንትነት መምረጥ መብቱ ነው። ይሁን እንጂ "እንደዚህ ዓይነቱን ከባድ ሃላፊነት የሚሸከም የአመራር አካል ምን መናገር እንደሚኖርበትና እንደማይኖርበት አስቀድሞ ይረዳ ዘንድ ግድ ነው።" የሚል እምነት አለኝ። አለበለዚያ  አሁን ዶ/ር መረራ እንደሚያደርጉት ቀልድ ይሁን ቁምነገር ለመለየት በሚያዳግት ፌዘኝነት ነባራዊውን እውነታ አድበስብሶ ማለፍን እንደ ፖለቲካዊ ጥበብ የሚቆጥር የፓርቲ መሪ በዘፈቀደ የሚሰነዝረው ፕሮፓጋንዳ ምናልባት ሀገር የሚያጠፉ እሳት ይጭርብን እንዲሆን እንጂ የተሻለ ነገር ያመጣል ተብሎ አይጠበቅም።

በእርግጥ እንዲህ ዓይነቱ የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅሞ እንዳመጣልህ የመናገር ችግር የዶ/ መረራ ብቻ እንዳልሆነ ይገባኛል። እንዲያውም  አብዛኞቹ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች በእጅጉ የሚመሳሰሉበት ጉዳይ ቢኖር ይሄው የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲባል በዘፈቀደ የሚሰነዘር አፍራሽ አቋም ማለት ይቻላል።

ለዚህ ደግሞ በ1997ቱ አገር አቀፍ ምርጫ ወቅት የቀድሞው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ አመራር አካላት የፈፀሙትን ታሪካዊ ስህተት ማስታወስ ተገቢ ይሆናል። እነርሱ በፖለቲካ ስካር ተገፋፍተው፣ "ወያኔዎችን ወደመጡበት እንመልሳቸዋለን" የሚል መፈክር በማሰማታቸው ምክንያት አንዳንድ በእውቀት ሳየሆን በስሜት የሚነዱ የአዲስ አበባ ወጣቶች፣ ጉዳዩን ወደለየለት ዘረኝነት ቀይረው "ትግሬ ወደ መቀሌ ንብረቱን ለቀበሌ" ማለት ጀምረው እንደነበር እናስታውሳለን።

ለመሆኑ ዛሬስ ለርለካሽ የፖለቲካ ትርፍ ሲባል በዘፈቀደ የሚሰነዘር መርዘኛ መልዕክት የዚችን ሀገር ህዝቦች ወዳልተጠበቀ የጋራ ጥፋት ሊወሰድ የሚችል ተመሳሳይ ታሪካዊ ስህተት ላለመፈፀም ምን ያህል ጥንቃቄ እየተደረገ ነው? ይ ጥያቄ ሊታሰብበትና ተገቢ ጥያቄ ማግኘት ይሻል።

ምክንያቱም የተቃዋሚ ፓርቲ ፖለቲከኞች አሁንም ለጠባብ የቡድን አጀንዳቸው መሳካት ሲሉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ጥላሸት መቀባታቸውን እንደ ጥበብ ሲቆጥሩት የሚስተዋሉበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም። ለምሳሌ ቅዳሜ ታህሳሰ 19 ቀን 2006 ዓ/ም የታተመው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ዶ/ር መረራ ጉዲናን ጨምሮ ሌሎችም የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አካላት ሲ.ፒ.ጄ ´ የተሰኘው የጋዜጠኞች መብት ተሚጋች ነኝ ባይ

ድርጅት በቅርቡ ያወጣውን ፀረ ኢትዮጵያ ሪፖርት ደግፈው የሰጡትን እጅግ አሳፋሪ ምስክርነት መመልከት ይቻላል።

መቀመጫው በአሜሪካ እንደሆነ የሚነገርለት ሲ.ፒ.ጄ  ለዓለም  ጋዜጠኞች መብት የሚሟገትና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ የሆነ  ተቋም ነው´ በሚል ሽፋን የሚንቀሳቀስ ድርጅት እንደሆነ ቢነገርለትም፣ ጸረ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስታዊ ሥርአት አቋም ያላቸው ቡድኖች የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ስለመሆኑ የ2013 ዓ.ም ሪፖርቱን በማየት ብቻ መረዳት የሚያዳግት አይመስለኝም። ይሄው "ገለልተኛ" ተብዬ ተቋም በተገባደደው የፈረንጆቹ 2013 ዓ/ም ኢትዮጵያ ጋዜጠኞችን በማሰር ከዓለም ሀገራት የሁለተኛነት ደረጃን እንደያዘች የሚያመለክት ሪፖርት ማውጣቱ ይታወቃል።

እናም ይሄው ሀገራዊ ገፅታችንን ለማበላሸት ያለመ የሲ.ፒ.ጄ መግለጫ ፈፅሞ ከእውነት የራቀና ተቀባይነት የሌለው ተራ የስም ማጥፋት ዘመቻ ስለመሆኑ የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት በሰጠው ምላሽ ሲያረጋግጥ፣ እዚህ አገር ውስጥ የሚገኙት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደግሞ "ትክክል ነው" የሚል አቋም ይዘዋል።

ከላይ ለመግለፅ እንደሞከረኩት ቅዳሜ ታህሳስ 19 ቀን 2006 ዓ/ም ታትሞ የወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ በጉዳዩ ዙሪያ ካነጋገራቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አካላት መካከል በተለይም የመድረክ ፕሬዚዳንት ዶ/ር መረራ ጉዲናና የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊው አቶ ዳንኤል ተፈራ የሰጡት ምላሽ ምን ያህል አስተዛዛቢ እንደሆነ አንባቢያን ትገነዘቡልኝ ዘንድ እነሆ እንደሚከተለው እጠቅሳለሁ።

"ለመሆኑ እዚህ አገርም ለጋዜጠኞች መብት መከበር  የሚሟገት የሙያ ማህበር አለ እንዴ !?´" ሲሉ የተለመደውን ፌዘኝነት የተጠናወተው ጥያቄያቸውን በማስቀደም ንግግር የጀመሩት ዶ/ር መረራ "እኛ እንደ መድረክ ኢትዮጵያ ጋዜጠኞችን በማሰር 2ኛ ናት መባሉን እንቀበላለን። እነ እስክንድር እነ ርዕዮትና እነ ውብሸት የታሰሩት እኮ ጋዜጠኞች በመሆናቸው እንጂ ሽጉጥ ሲሰርቁ ተገኝተው አይደለም። ስለዚህ የሲ.ፒ.ጄ ሪፖርት በትክክለኛ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ነው የሚል እምነት አለን" ብለው አጠቃለዋል ።

ከእርሳቸው በመለጠቅ  ለአዲሰ አድማስ ጋዜጣ አስተያየት የሰጡት የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊም ቢሆን ከመድረኩ ፕሬዚዳንት እንብዛም የተለየ ሃሳብ አቅርበዋል ለማለት ያዳግታል። ምናልባትም የዶ/ር መረራን

ንግግር ለማጠናከረ ሲባል ብቻ የተጠየቀ እስኪያስመስልበት ድረስ የሲ.ፒ.ጄ.ን ሪፖርት ተአማኒነት ለማላበስ ነው የጣሩት።

“በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ተችተው የሚፅፉ የግሉ ፕሬስ ጋዜጠኞች ሽብርተኛ እየተባሉ ለእስር የሚዳረጉባት እንዲሁም የሚደርስባቸውን ተፅእኖ መቋቋም ሲያቅታቸው አገር ጥለው ለመሰደድ የሚገደዱባት፣ ጋዜጦች በየጊዜው እንዲዘጉ የሚደረጉባት ኢትዮጵያ አይደለች እንዴ!?” ከሚል የመገረም ጥያቄ ጋር  ለሲ.ፒጄው ሪፖርት ያላቸውን ድጋፍ የገለፁት አቶ ዳንኤል ፓርቲው አስቀድሞ ያስጠናቸውን ቃለ ተውኔት ነው የደገሙልን፡፡

“የሲ.ፒ.ጄ. ሪፖርተ እኮ በብዙ ጥናታዊ መረጃዎች ታግዞ ነው እንጂ የሚወጣው ስለጉዳዩ ምንም ዓይነት ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች እንደሚሉት ዝም ብሎ ከባዶ ነገር ላይ የሚነሳ አይደለም” ሲል ከአጉል ብልጣብልጥነት በመነጨ የውግዘት ፖለቲካው “ጀንጅነው” ሊያሳምኑን መድከማቸው፣ ቢያንስ ትዝብት እንኳን አለመፍራት ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ለምን ቢባል ተቃዋሚዎች ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩለት ሲ.ፒ.ጄ የተሰኘ ባህር ማዶ የሚገኝ ተቋም ከእነማን ጋር ወግኖ እንደሚዶልትብን አሳምረን እናውቃለንና ነው። ስለዚህም “ሪፖርት” ተብየው ከገለልተኛ ምንጮች በተገኘ ታማኝ መረጃ ተደግፎ የቀረበ ሊሆን ቀርቶ ምንም ዓይነት የኢትዮጵያን ወቅታዊ እውነታ የሚያመለክት ይዘት ያልተካተተበትና በለየለት የጥላቻ ፖለቲከኞች ጭፍን ውግዘት ላይ የተመሰረተ የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው ቢባል የተሻለ የሚገልፀው መስሎ ይሰማኛል።

ምክንያቱም “የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች” ተብየው ሲ.ፒ.ጄ አፈቀላጤው አድርጎ ያስቀመጠው ክፍሌ ሙላት የተባለ ኢትዮጵያዊ ማን እንደሆነ አብጠርጥረን ለመናውቀው የዚች አገር ዜጎች “ሪፖርቱ ገለልተኛ ነው” ብሎ ለማሳመን መሞከር በእርግጥም ትዝብት አለመፍራት እንጂ ሌላ ስም ሊገኝለት አይችልም። ክፍሌ ሙላት ማለት እስከ ምርጫ 97 “ልሳነ ህዝብ” የተሰኘ የግል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና የኢትዮጵያ “የነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር” በመባል ይታወቅ የነበረውን ማህበር በፕሬዚዳንትነት ሲመራ የቆየ ሰው የመሆኑ ጉዳይ ፀሐይ የሞቀው እወነት ነው።

አቶ ክፍሌ ሙላት በ97ቱ ምርጫ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ ከሞከሩት የቅንጅት አመራር አካላት ጋር አሲሮ እንደተንቀሳቀሰና ውጥናቸው ሲከሽፍም በኬንያ በኩል ሸሽቶ ከሀገር እንደወጣ ይታወቃል፡፡የስደት ጉዞውን ወደ ኡጋንዳ በማራዘምም ካምፓላ ውስጥ ለሲ.ፒ.ጄ የፈጠራ ወሬ አቀባይ ሆኖ ሲያገለግል ነበር፡፡

እንግዲህ ይህ ሰው ነው የጋዘጤኝነት ሙያ ስነምግባር ከሚፈቅደው ውጭ የፈጠራ ወሬ ለማቀበል ያስቻለውን አጋጣሚ ተጠቅሞ በሀገሩ መንግስት ላይ ያደረበትን ቂም ለመወጣት ሲል የኢትዮጵያን ፈርጀ ብዙ የህዳሴ ጉዞ ጥላሸት ለመቀባት እንቅልፍ አጥቶ የሚያድረው፡፡ ሲ.ፒ.ጄ በእርሱ የፈጠራ ወሬ ላይ ተመስርቶ የሚያቀርበውን ዓመታዊ “ሪፖርት” ተብዬ ወሬ ፈረንጆቹ አምነው ይቀበሉት ዘንድም የሀገር ውስጥ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሐሰት ምስክርነት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በነገራችን ላይ የኛ ሀገር ተቃዋሚ ፓርቲዎች “ለሚያልፍ ቀን የማያልፍ ቃል አትናገር” የሚለውን ጥቅስ ያወቁት ይሆን!?